# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራያዊ ሪፐብሊክ

## የኢትዮጵያ ብኄራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ

## የ2014 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት/2015

**አዲስ አበባ**

# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራያዊ ሪፐብሊክ

# የኢትዮጵያ የኢትዮጵያ ብኄራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ

# የ2014 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት

የኢትዮጵያ ብኄራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ የተመደበለትን የመደበኛ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የየኢትዮጵያ ብኄራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው ::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን ዓለም አቀፍ የዋና ኦዲተሮች የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

**ኦዲታችን፡-**

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑንና በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ኤጀንሲው ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች ፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በኤጀንሲው ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ ሪፖርት ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዞ ቀርቧል፡፡

- የተጠቃለለ ሂሳብ ማመዛዘኛ፣

ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ የ2014 የሂሣብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት በመንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁና፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን ጠብቆ የተከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

ወጪ፤

1. በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 አንቀፅ 8 ንዑስ አንቀፅ 2 ፊደል ለ ላይ "ወጪ ከመደረጉ በፊት ስለወጪው የተሟላ ማስረጃ መቅረብና ስልጣን ባለው አካል መፈቀድ አለበት ይላል፡፡እንዲሁም የመንግስት ሰራተኞች የአገር ውስጥ የቀን ውሎ አበል መመሪያ የካቲት/2012ዓ.ም አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀፅ 2 "የቀን ውሎ አበል" ማለት አንድ የመንግስት ሰራተኛ በአገር ውስጥ ከመደበኛ የስራ ቦታ ወደ ሌላ የስራ ቦታ ለስራ ጉዳይ ሄዶ በዕለቱ ለመመለስ ሳይችል ሲቀር ለሚያስፈልገው የምግብ እና የመኝታ ወጪ የሚከፈል አበል ነው በማለት ይገልፃል፡፡በመሆኑም ከፍያዎች ህግን ተከትለው ስለመፈጸማቸው ለማረጋገጥ በተወሰደ የኦዲት ናሙና፤
   - ከቀን 3/13/2013 ጀምሮ ለተከታታይ 15 ቀናት የመስሪያ ቤቱ ሰራተኞች ስልጠናውን ለ15 ቀናት ሰልጣኞች እንደወሰዱ ተደርጎ የውሎ አበል በድምሩ ብር 1,208,765 የተከፈለ እና የ14 የአዳራሽ ኪራይና ሪፍረሽመንት በነጻ የተከናወነ ቢባልም ከወጪ ሰነዱ ጋር የሰዓት መቆጣጠሪያ ያልቀረበ በመሆኑ፤ ስልጠናው ስለመከናወኑ በሚመለከተው አካል በፊርማ ያልተረጋገጠ በመሆኑ፤ሆቴሉ ለአስራ አራት ቀናት ሪፍረሽመንት እና አዳራሽ በነጻ ስለመሆኑ የሆቴል የአገልግሎት ውል ለኦዲት አለመቅረቡ እና ወጪው አስቀድሞ አገልግሎት ከመሰጠቱ በፊት ውሎ አበሉ ተከፍሎ መገኘቱ፤
   - በደረሰኝ ቁጥር 0005748 በቀን 26/8/2014 ብር 237,920.00 በሂሳብ መደብ 2221101 በመደ ወላቦ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር በሮቤና ጎባ ከተሞች ከሚያዚያ 29 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ መዛግብትና የጽሁፍ ቅርሶች ለዘመን ትውስታ በሚል መሪቃል ለተከናወነው ቡክ ፌር ላይ ለተሳታፊዎች የውሎ አበል

ክፍያ እንዲፈጸም ሲደረግ ወጪው በውሎ አበል መጠየቂያና ማወራረጃ ቅጽ ያልተዘጋጀለት በመሆኑ ሂሳቡ በአግባቡ መወራረዱን ማረጋገጥ አለመቻሉ፤

- የንብረት ስራ ክፍልና የተሽከርካሪ ስምሪት የውስጥ አሰራር መመሪያ ላይ ውይይት የማድረግና የማነቃቂያ ስልጠና ከሚያዚያ 4 ቀን 2014 ጀምሮ ለ14 ቀናት በአዳማ ከተማ ለማከናወን ብር 571,326.00 ክፍያ ሲፈጸም፤የስልጠናው የክፍያ ሰነድ ያልተዘጋጀና የሰአት መቆጣጠሪያው በሚመለከተው አካል ያልጸደቀ መሆኑ፤ ለስልጠና የሚያስፈልገውን የመስተንግዶና የአዳራሽ ኪራይ ክፍያ ሰነድ የሌለ መሆኑ ፤ ስልጠናው ሳይጠናቀቅ ክፍያው በወጪ እንዲመዘገብ የተደረገ መሆኑ ::
- በባህርዳር ከተማ የንባብ ሳምንት ቡክ ፌር እና ኤግዚቢሽን ተሳታፊዎች ብር 199,710.00 ለተፈጸመው የውሎ አበል ክፍያ የውሎ አበል መክፈያ ሰነድ ያልተዘጋጀ መሆኑ፤ ከውጪ የተጋበዙ ተሳታፊዎች የጥሪ ደብዳቤ ያልቀረበ በመሆኑ የሚከፈላቸውን የውሎአበል ለመተመን የሚያስቸግር መሆኑ፤ በወጪማዘዣው ላይ የውሎ አበል የመነሻ ቀን እንጂ የመመለሻውን ቀን ያልተገለጸ በመሆኑ፤ ጉዞው ምን ያህል ቀን እንደፈጸሙና የምን ያህል ቀን ታስቦ እንደተከፈለ ባልታወቀበት ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፡፡
- ብር 165,972 ለተፈጸመው ክፍያ፤ በተመለከተ፤የክፍያ ሰነዱ በሚመለከተው ሃላፊ ያልጸደቀ ከመሆኑ በተጨማሪም የውሎ አበል ክፍያ ማወራረጃ ሰነድ በመመሪያው መሰረት ያልተዘጋጀ ሆኖ መገኘቱ፤ የውሎ አበል መጠየቂያ ሰነድ ላይ ለስራ የተሰማሩበት ቀን ከመቼ እስከመቼ እንደሆነ የተገለጸ ባለመሆኑ የማወራረጃ ሰነዱ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ያለመቻሉ፤የክፍያ ሰነዱ ያረጋገጠው እና ያጸደቀው አንድ ሰው መሆኑ ::

በጠቅላላ ድምር ብር 2,383,693.00 ለተፈጸመ ክፍያ በቂ የሆነ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

2. የፌዴራል መንግስት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 ክፍል ሁለት የፋይናንስ ኃላፊነት የመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ቁጥር 6(ለ) የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ላይ በመመርኮዝ በወጡት መመሪያዎች በመ/ቤት ውስጥ በተሟላና ተገቢ በሆነ መንገድ ሥራ ላይ መዋላቸውን በማረጋገጥ ረገድ

ተጠያቂነት እንዳለባቸው ይገልፃል፡፡ እንዲሁም የኢትዮጵያ ፌደራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ ሥራዓት ግንቦት 1999 ዓ.ም በወጣው የሂሳብ መደብ የተሰጠ ትርጉም ይህ የወጪ መደብ በንግድ ሥራ ከተሠማሩ ድርጅቶች እና ግለሰቦች በመንግስት ባለቤትነት ስር ወይም ከመንግስት ውጭ ካሉ ተቋሞች ጋር የሚደረግን የሙያ አገልግሎት ውልን ያካትታል በማለት ይገልፃል:: በዚህ መሠረት በውልብር181,543.00 ክፍያ የተፈጸመበት ሰነድ መመሪያው መተግበሩን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- በመስሪያ ቤቱ ውስጥ ለሚከናወን ስልጠና እንዲሰጡ የሚጋበዙት አሰልጣኞች ስለመጋበዛቸው እና ማንነታቸውን የሚገልጽ ማስረጃ የማይቀርብ መሆኑ
- ስልጠናውን ለመስጠት የሚችሉ ስለመሆናቸው የትምህርት ዝግጅት ወይም የተለየ ተሰጥኦ ያላቸው ስለመሆኑ የሚያስረዳ ምንም አይነት ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ ፡፡
- በውል ለሚፈጸም ክፍያ ተገቢ የሆነ በህግ በኩል ተቀባይነት ያለው ውል በከፋይና አገልግሎት ከሚሰጠው አካል ጋር እንዲሁም ምስክሮች ባሉበት በፊርማ የማይረጋገጥ መሆኑ ፡፡
- ውል የተገባበት ጉዳይ ምን እንደሆነ በውሉ ውስጥ የማይገለጽ መሆኑ ፡፡
- ለሚጋበዙት ባለሙያዎች የሚከፈለው ክፍያ የገንዘብ መጠን ወጥነት ያሌለው ከመሆኑ በተጨማሪም የሚከፈለው ገንዘብ መጠን በበላይ አካል ያልጸደቀ መሆኑ፡፡
- አሰልጣኞች በአሰልጣኝነት ለቆዩበት ግዜ ከውል ከተዋዋሉት በተጨማሪ የስልጠና አበል ዉይም የውሎ አበል ታስቦ የሚከፈላቸው መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 2 ከተገለፁት በስተቀር የመ/ ቤቱ የሂሳብ ሪፖርቶች በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ የተሰበሰበውን ገቢ የተከፈለውን ወጪና የበጀት አጠቃቀም በአጥጋቢ ሁኔታ ያሳያሉ፡፡

**ህጋዊነትን ያልተከተሉ ጉዳዮች (Compliance Matters)**

**ገቢ፤**

3. የፌደራል መንግስት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር3/2003 በአንቀጽ 22 የመንግስት ገቢ አሰባሰብ አንቀጽ 22 ንኡስ አንቀጽ 3 ላይ የመንግስት ገንዘብ ሊሰበሰብ የሚችለው ተከታታይ ቁጥር ባለውና ሚኒስተሩ ባሳተመው የገቢ ደረሰኝ ወይም በሚንስትሩ ፈቃድ በሚዘጋጅው የገቢ ደረሰኝ ወይም ኤሌክትሮኒክስ ገንዘብ መሰብሰቢያ ዘዴ መጠቀም እንደሚቻል፤እንዲሁም በሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር 378/2008 ታሪፍ ባወጣው ደንብ መሰረት መሰብሰብ እንዳለበት በተደነገገው መሰረት ተግባራዊ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ በተወሰደ የኦዲት ናሙና ፡፡

   - የገቢ ደረሰኙ ገንዘብ ሚኒስቴር ባሳተመው የገቢ ደረሰኝ አለመሆኑና መ/ቤቱ በራሱ ስም በታተመው የገቢ ደረሰኝ የሚጠቀም መሆኑ፤
   - በኤጀንሲው ብር28,206.02 ለተሰበሰበወው ገቢ ተገቢ መረጃ ባለመቅረቡ ገቢው በታሪፉ መሰረት ስለመሆኑ ለማረጋገጥ አለመቻሉ በኦዲት ታውቋል፤

**ተሰብሳቢ ሂሳብ፤**

4. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሠራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ ፤በመመሪያ ቁጥር 5/2003 መሠረት ደግሞ ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል፡፡ ይሁንና መ/ቤቱ ተሰብሳቢ ሂሳቦች በደንቡና በመመሪያው መሰረት በወቅቱ እንዲወራረዱ ተገቢው ክትትል ለመደረጉ ሲጣራ፤

   - በሂሳብ መደብ 5217301 የተንጠልጣይ ሂሳብ ብር8,255.25 ክፍያው መቼ እንደተፈጸመ የማይታወቅ ፡ ገንዘቡ ከማን እንደሚሰበሰብና መቼ እንደሚወራርድ የማይታወቅ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

**ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች(Emphasis matter)**

**ወጪ**

5. ሂሳቦች የሚያዙትና የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ በተወሰደ የኦዲት

ናሙና በሀገር መከላከያ ሚስቴር በኩል ለተፈናቀሉ ዜጎች እርዳታና ድጋፍ የሚሆን ገንዘብ በሂሳብ መደብ 2631101(6412) መመዝገብ ሲገባው በሂሳብ መደብ 2221103 /6233/ በቀን 12/4/2014 በሰነድ ቁጥር-4953 በብር 300,000.00 ያለአግባብ ተመዝግቦ ተገኝቷል ፡፡

**በጀት፤**

6. የፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል ሶስት አንቀጽ 12(1) ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ለበጀት አመቱ የተፈቀደለትን የመደበኛ በጀት አጠቃቀም በሚገባ መቆጣጠር እንዳለበት በተደነገገው መሰረት መስሪያቤቱ ተግባራዊ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ በፕሮግራም ከተደለደለው በጀት ከ10% በላይ ሲታይ፤

   የመደበኛ በጀት ብር 19,050,547.55 ስራ ላይ ያልዋለ በጀት መኖሩ ታውቋል፡፡

**ሌሎች ጉዳዮች(Other matter)**

**የንብረት አመዘጋገብ፣ አያያዝ እና አጠባበቅ፣**

7. የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ክፍል አንድ አንቀጽ 5 የመመሪያው አላማ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በእጃቸው ያለውን የመንግስት ንብረት በጥንቃቄ የመያዝ፣ የመጠቀም፣ የመቆጣጠር እና አገልገሎት ላይ በማይውልበት ጊዜ በወቅቱና በተገቢው መንገድ ማስወገድ እንዳለበት ያዛል። ይሁን እንጂ ኤጀንሲው ያለውን ቋሚና አላቂ ንብረት በቁጠባና በአግባቤ ስለመጠቀሙ ለማረጋጥ ኦዲት ሲደረግ

   - ቀን 2/12/2014ዓ.ም በቁጥር 5/3-03 በተፃፈ ደብዳቤ ልዩ ልዩ የኮምፒውተር ከነአክሰሰሪው እንድወገዱ የተፃፈ ቢሆንም እሰከ አሁን ያልተወገደ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል።
   - በቤተመፀሐፍት የሚገኙ መጽሀፍቶች መዛግብቶችና የብራና ጽሁፎች እንዲሁም ቅርሶች ቆጠራ ተደርጎ የማያውቅ መሆኑ በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡

**የክትትል ኦዲት**

8. የፌዴራል ዋና ኦዲተር በ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ መግለጫዎችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርጎ ሙያዊ አስተያየትና የማሻሻያ ሃሳቦች ያቀረበ

ሲሆን፣ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ የተወሰደባቸውና ያልተወሰደባቸው ግኝቶች ሁኔታ ሲጣራ፡

በኦዲት አስተያየቱ መሰረት በቁጥር ደረጃ ከተገለጹት የአሰራር ክፍተቶች ውስጥ 50% እርምጃ የተወሰደበት ሲሆን 50% እርምጃ አልተወሰደበትም፡፡በገንዘብ ደረጃም እርምጃ ሊወሰድበት ከሚገባው አጠቃላይ የገንዘብ መጠን ውስጥ 0%ላይ እርምጃ የተወሰደበት ሲሆን 100% እርምጃ ያልተወሰደበት መሆኑ ታውቋል፡፡ ይኸውም፡

- ብር 3,119.14 መ/ቤቱን ለለቀቀ ሰራተኛ የተከፈለ
- ብር 91,714.75 ከመመሪያ ውጭ የተከፈለ ውሎ አበል
- 2,109,004.51 የግንባታ ሂሳብ በ ተመለከተ
- 8,255.25 ከማን እንደሚሰበሰብ የማይታወቅ
- የገቢ ሂሳብ አሰባሰብ
- ንብረት በተመለከተ
- በጀት አጠቃቀም

ከሰላምታ ጋር

**የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት**